Orange

የድሬዳዋ አስተዳደር ከውንስል

የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና

መቆጣጠሪያ ምክር ቤት

ረቂቅ መርሃ ግብር

ማ ዕ ቀ ፍ

CCRDA

የካቲት 1993 ዓ.ም

ድሬዳዋ

መ ግ ቢ ያ

እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር በ 1980 አካባቢ በአሜሪካን ሀገር የታየው የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ እነሆ በአሁኑ ወቅት ወደ 36 ሚሊዮን የሚጠጋ የአለማችንን ሕዝብ እያጠቃ ይገኛል።

በኢኮኖሚ እድገቷ ወደ ኋላ የቀረችውና በአለም ካሉ ደሀ ሀገሮች የምትመደበው ሀገራችንም ውስጥ ይህ አስከፊ ወረርሽኝ ከታየበት ከአለፉት አስርት ዓመታት ጀምሮ እስከ አሁን ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ ጋር አብሮ እንደሚኖር በርካታ ዘገባዎች ያመለክታሉ። በዚህ በሽታ የበለጠ ተጠቂዎች ሆነው የሚገኙት እድሜያቸው ከ 15 እስከ 49 አመት የሆኑ ዜጎች ናቸው። ድህነታቸንን ለመቅረፍ ትግል እየተደረገ ባለንበት ባሁኑ ወቅት ይህ ህይወት ቀጣፊ በሽታ መከሰቱ የወደፊት ጉዟችንን እጅግ አዳጋች አድርጎብናል።

ይህን ወረርሽኝ ለመግደብ በየደረጃው እንቀሰቃሴ እየደረግን ብንሆንም ከችግሩ አሳሳቢነት ውስብስብነትና አጣዳፊነት አንፃር ብዙ እጅግ ብዙ ትግል እንደሚጠብቀን አይካድም። በየግዜው በአስከፊ ሁኔታና በፍጥነት እያዳረሰን፤ እየወረረን የሚገኘው ኤች አይ ቪ ኤድስ ከጤና ችግርነቱ አልፎ የልማትና የእድገት እንቅፋት ሆኗል።

እንደማንኛውም ክልል በድሬዳዋ ኤች አይ ቪ ኤድስ በግለሰብም ሆነ በህብረተሰቡ ላይ እጅግ ሰፊ የሆነ ማህበራዊ፤ ሥነ ሕዝባዊ ፤ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቦናዊ ቀውስ እያሳደረ ይገኛል። ይህ ወረርሽኝ በግለሰብ ላይ ከሚያደርሰው ስቃይና ሞት ባሻግር፤ ለትዳር መፍረስ ፤ ለቤተሰብ መበታተን፤ ሕፃናትን ያለአሳዳጊ ማሰቀረት የመሳሰሉ ማህበራዊ ችግሮችን እያባባሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት ፤ ችግሩን ለመግታት በጋራ መንቀሳቀስ የሚቻልበትን ማንኛውንም ዘዴ መጠቀም ትክክለኛ አቅጣጫ እንደሆነ መስተዳደሩ ያምንበታል።

ይህንን የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ቤት እያንኳኳ ያለ በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድና መንግስት እያደረገ ያለውን ሁሉ አቀፍ አንቅስቃሴ ለማጎልበት በእስተዳደር ካወንስላችን የሚተገበር መርሃ ግብር ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል።

CCRDA

በዚሁ መሰረት ወደፊት ኤድስ ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት ለመከላከልና ለማቆጣጠር በበሽታው ተይዘው ያሉና ከቫይረሱም ጋር አብሮ የሚኖሩ ሰዎችን እንደዚሁም በዚሁ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ህፃናት ከመርዳት አንፃር መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የተለያዩ ተቋማት የሚመሩበት ረቂቅ መርህ ግብር /ማዕቀፍ/ ተዘጋጅቷል ። መርሃ ግብሩ በውስጡ የተለያዩና በርካታ ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን መላው የህብረተሰብ ክፍል በጋራ በመረባረብ ለተግባራዊነቱ እንደሚንቀሳቀስ ይጠበቃል።

1. የድሬዳዋ አስ/ካው /ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት መርሃ ግብር ያከተታቸው ሰነዶች፤

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለ 1990 ዓ/ም ያወጣው ብሄራዊ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ፤
2. በ 1985 ዓ /ም የወጣው የሀገሪቷ አጠቃላይ የጤና ፖሊሲ፤
3. ብሄራዊ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በ 1993 ዓ/ም ያወጣው ረቂቅ መርሃ ግብር፤
4. የአለም ባንክ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የተስማማበት የብድር ውል ሰነድ / 1993 ዓ/ም/፤
5. የሀገሪቷ ቀጣይ የ 5 አመት መሪ የልማትና መርሃ ግብር ፤
6. የአለም አቀፍ ሕፃናትና እናቶች አድን ድርጅት ሰነድ፤
7. በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል አደጋ መከላከልና ዝግ/ኮ/ሰመጉ ጽ/ቤት ድሬዳዋና ማህበራዊ ችግሮቿ የተሰኘ ጥናት ሪፖርት፤

8. በድሬዳዋ በተለያዩ ወቅቶች በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች ሪፖርቶችን የተዳሰሱ ሲሆን ፤ ሌሎች መስተዳደር ካውስሉ ውስጥ በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ የተደረጉ ዘገባዎችን እንደዚሁም በየወቅቱ የሚታተሙ ፅሁፎችን በአጋዥነት ለመጠቀም ተሞክራል፡

ከላይ የተጠቀሱት ሰነዶች የሀገሪቷን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን፤ ማህበራዊ ነክ አላማዎችን የሕፃናት መብቶች፤ የሴቶችን እኩልነትና የጋበቻና የቤተሰብ ሕግጋትን ለማዛመድ የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን ለዚህ መርሃ ግብርም ዝግጅት ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው።:

CCRDA

2 ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በድሬዳዋ አስከ አሁን ምን ጥረቶች ተካሂደዋል?

2.1 ቀደም ሲል በክልላችን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆከውንስልና ሴክሬታሪያት ከመቋቋሙ በፊት በክልሉ ሲደረጉ የቆዩትን የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች የማስተባበር ሃላፊነት ለጤና ጽ/ቤቱ የተሰጠ ሃላፊነት ነበር በመሆኑም በተለያዩ አካላትና መድረኮች የትምህርት ሰርአትና መረጃ ልውውጥ ጥረቶች ተካሂደዋል። ይህም በት/ቤቶች ወጣት ተማሪዎችን በኤች አይ ቪ ዙሪያ በርካታ መድረክና በተለያዩ ባለሙያዎች ትምህርት ተሰጥቷል ክት/ቤት ውጭም ላሉ ሴትና ወንድ ወጣቶችን የኤች አይ ቪ ኤድስ ምንነትን፤ የመተላለፊያ መንገዶችን መከላከያ ዘዴዎችንና ኤች አይ ቪ የማይተላለፍበትን መንገዶች በውይይት ፤ በድራማና ትያትር በዕሁፍና መዝሙር በመሳሰሉት ዘዴዎች ትምህርት ሲሰጥ ቆይቷል።

2.2 በትምህርት ቤቶችና በቀበሌ አከባቢ ዐረ ኤድስ ክበባት ተመስርተዋል።ለነዚህም ክበባት ከዊብስና ከዩኒሴፍ አገር አቀፍ ኘሮግራም በተገኙ ድጋፎች እንዲጠናከሩ ጥረት ተደርጉል።

2.3 አመርቂ ባይሆንም ከኤች አይ ቪ ቫይረስም ጋር ለሚኖሩ ሰዎች አስፈላጊውን የድጋፍና የእንክብካቤ ስራ ከ OSSA ጋር በመተባበር ተከናውኗል።

2.4 ከሰኔ 1992 ጀምሮ በክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ ሴክሬታሪያት የተቋቋመ ሲሆን ዋና ተግባሩም በተለያዩ አከላት በክልሉ የሚደረጉትን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎችን የማስተባበርና የማቀናጀት ነው። በመሆኑም ሴክሬታሪያቱ ከተቋቋመ ጀምሮ ባብዛኛውን ራሱን በሰው ሃይልና በቁሳቁስ በማደራጀት ላይ ቢሆንም ከተባበሩት መንግስታት የእናቶችና ህፃናት መርጃ ድርጅት ጋር በመተባበርና ድጋፍ በማግኘት አራት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ክልላዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ ኘሮግራም እቅድ ተሰርቶ ኘሮግራሙና የማስፈፀሚያ ባጀቱ ፀድቆ የመጣ ሲሆን ንዑሳን ኘሮግራሞቹም፡

1. ወጣቶችንና የወጣት ቡድኖችን ክበባትን በማስተባበር ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ፤
2. ለኤች አይ ቪ ታማሚዎች ድጋፍና እንክብካቤ መስጠት፤
3. ከእናት ወደ ልጅ የኤች አይ ቪ ኤድስ መተላለፍን መከላከል ፤
4. ዝምታውን ሰብሮ የፀረ ኤድስ ቅስቀሳ ስራዎችን ማካሄድ በሚሉ ዋና ዋና ጉዳዩች ላይ ያተኩሩ ናቸው።

ከላይ በተጠቀሰው የኘሮግራም እቅድ ዝግጅት ሂደት በክልሉ የሚገኙ የኘ ሮግራሙ ፈጻሚ መ/ቤቶች የተሳተፉበት ሲሆን ለኘሮግራሙ ተግባራዊነት የፈጻሚ መ/ቤቶች የተቀናጀና የጋራ እንቅስቃሴ ይጠበቃል።

CCRDA

2.5 በትርቡ የኢትዮጲያ መንግስት ከአለም ባንክ ጋር በተፈራረመው የብድር ስምምነት የ 3 ዓመት የኤች አይ ቪ/ኤድስን በሽታ የመከላከልና የመቆጣጠር ኘሮግራም የተነደፈ ሲሆን ክልላችንም የዚህ ኘሮግራም ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ከብሔራዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ክልላዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ እቅድ ተሰርቶ እንዲላክ በተጠየቀው መሰረት በክልላችን ያሉ መንግስታዊ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ስለጉዳዩ በተደረገላቸው ገለፃ መሰረት እቅድ ሰርተው እንዲያቀርቡ ተገልያላቸው በእቅድ ዝግጅት ላይ ሲሆኑ ሁሉም ፈጻሚ መ/ቤቶች እቅዶቻቸውን አጠቃለው ሲያቀርቡ በቀረቡት እቅዶች ላይ ተገቢው የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ ለጠያቂው አከል እንደሚላክ ይጠበቃል።

2.6 በአጠቃላይ የያታአኩልነት ባማክለ ሁኔታ ማንኛውንም ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሰራ እንዲካሄድ እሰፈላጊውን ትኩረት በመስጠት እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያ የሚካሄዱ ጥናቶች እንዲበረታቱ ይደረጋል።

2.7 በክልል ደረጃ የ 5 ዓመት የጤና ሴክተር የልማት ኘሮግራም የተዘጋጀ ሲሆን በዚህም ውስጥ የኤች አይ ቪ ኤድስ አንዱ የኘሮግራም አከል ነው።

3 የድሬዳዋ ጤና ሽፋን ምልከታ

እንደሚታወቀው በ 1986 ዓ/ም በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ የሀገራችን ሕዝብ ብዛት 63 ሚሊዩን አንደሆነ ይገመታል። የድሬዳዋ አስተዳደር ከውንስል ነዋሪ ሕዝብ ብዛት 308.438 ሲሆኑ 50.5/ ወንደች እና 49/ ሴቶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ 71/ የከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ 29/ ያህሉ የገጠር ነዋሪዎች ናቸው። አስተዳደር ከውንስሉ 1977 ስኩየር ኪሎ ሚትር የቆዳ ስፋት ያለው ሲሆን ማደረጃጀቱም 25 ቀበሌዎች በከተማ 29 ቀበሌ ገበሬ ማህበራት በገጠር ያከተተ ነው። የአስተዳደር ከውንስሉ ነዋሪ በአመዛኙ የከተሜነት ባህሪ ያለው ሲሆን ድሬዳዋ አመሰራረቷ ከንግድና ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ጋር ቀጥታ ግንኙነት እንዳለው በርከታ ፅሁፎች ይገልፃሉ።

- የድሬዳዋ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን በ 1987 ዓ ም 35 የነበረው በ 1991 ዓ/ም 63% ሲሆን ሁለት ሆስፒታሎች አንድ የኢትዮ ጅቡቲን ጨምሮ 320 የሚደርሱ አልጋዎች አሏቸው።
- በአጠቃላይ 20 ሀኪሞች ፤ 70 ነርሶች 15 የላባራቶር ቴክኒሽያናች አሉ።
- አንድ ሀኪም ለ 15,426 አንድ ነርስ ለ 4,406 ሰዎች
- በሰለጠነ ባለሞያ የተሰጠ የወሊድ አገልግሎት 27% ፤

CCRDA

- የጤና አገልግሎት ሽፋንና የባለሙያ ስርጭት የተሻለ መስሎ ቢታይም በአብዛኛው በአንራባች ክልሎች ነዋሪዎች መታከሚያ ጭምር በመሆኑ ይህ የሽፋን ደረጃ ሙሉ በሙሉ የክልሉን ነዋሪ ፍላጉት አስተናግዳ ማለት አይቻልም።

- በተመላላሽ ተመዝግበው ከታከሙት ህመሙን ውስጥ 9.8% በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ሲሆን ተኝተው ከታከሙት በሽታዎች በአጠቃላይ 17.6% የዚሁ በሽታ ተጠቂዎች ናቸው። ስለዚህ በሁለቱም አይነት የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በደረጃ ከመጀመሪያዎቹ 10 የበሽታ ዝርዝር የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ባለፉት 5 አመታት ተኝተው ከታከሙት በሽተኞች መካከል በየአመቱ መጨመር ከ5% ወደ 25% አድጓል።

ከበሽታው አዝጋሚ የመዳን ሂደት አንጻር ተኝቶ በመታከም የሚወሰደው ጊዜ የሆስፒታሉን አልጋ ለሌች በሽተኞች መጠቀሚያ እንዳይውል እያደረገ መምጣቱን በግልጽ ይታያል።

ከዚህ በተጨማሪም በየጤና ተቋማቱ ያለው አገለግሎት የመስጠት ብቃት አናሳ መሆን ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች ጋር ተዳምረው ችግሩን አያባብሰው ይገኛል።

ይህ የሚያሳየን ኤች አይ ቪ ኤድስ ከሌሎች በርከታ ምክንያቶች ጋር በተዘዋዋሪ እየተስፋፋ የመጣ ችግር መሆኑን እና ሃለው ውሱን የጤና አገልግሎት ብቃትና የጤና አጠባበቅ በጀት አቅም ጋራ በጤና አገልግሎቱ ላይ እያደረሰ ያለው ጫና በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑን ነው።

4 ኤች አይ ቪ ኤድስ በድረዳዋ አስተዳደር ካውንስል ምን አይነት ገፅታ አለው?

እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር በ 1992 / 93 ለቅድመ ወሊድ ምርመራ ለማድረግ በመጡ ነፍሰ ጡር እናቶች ላይ ሆስፒታል ውስጥ በተደረገ ምርመራ 12.6% ያህሉ የቫይረስ ተጠቂ ሆነው የተገኙ የነበረ ሲሆን እንደገና በ 1999/ 2000 በተያዘው መረጃ መሰረት 13.6% ያህሉ እናቶች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሆነው ተገኝተዋል። እንደዚሁም በ 1992 ዓ/ም ደም ለመለገስ በ 678 ሰዎች ከተሰጠው ደም 67 ያህሉ 10% ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሆነው መገኘቱንም ዘገባዎች ይጠቁማሉ።

የኤድስ በሽታ ስርጭቱ የተመለከትን እንደሆነ ከ1990 -1992 በሦስቱ ዓመት የተወሰደው መረጃ እንደሚያመለክተው የመጨመር አዝማሚያ ነው የሚያሳየው ይህም በ1990 ዓ/ም ተጠቂዎች ቁጥር በጠቅላላው 227 ሲሆን ወንድ 85 (37.4/) ሴት 142 (62.5/) በ1991 በጠቅላላው 240 ወንድ 114 (47.5/) ሴት 126 (52.5/) ሲሆን በ1992 በጠቅላላው 260 ወንድ 133 (51.20/) ሴት 127 (48.8/) ነው ከዚህም የምንረዳው በ1990 227 የነበረው ቁጥር 1992 ወደ 260 ከፍ ያለ ሲሆን በፐርሰነት 14.5 ጭማሪ አሳይቷል።

CCRDA

4 - በድሬዳዋ ኤች አይ ቪ ኤድስን በመከላከል ዙሪያ ከዚህ በፊት የነበሩ ችግሮች፤ ዋና ዋናዎቹ፤

5.1 - ኤች አይ ቪ ኤድስ የጤና ችግር ብቻ ሣይሆን አጠቃላይ የልማት ችግር መሆኑን ከለመገንዘብ የሚመለከታቸውን አከላትና ሕብረተሰቡን ያሳተፈ፤ የተቀናጀና የቀጥጥር ስራዎችን የሚመራ የተጠናከረ ድርጅታዊ መዋቅር አለመኖር፤

5.2 - በክልሉ የበሽታውን መጠንና ሥርጭት ሁኔታ በትክክል ለማወቅ የተደረጉ ጥናቶች አነስተኛና አስተማማኝ አለመሆን እንደዚሁም መደበኛ የሆነ የመረጃ ትንተና ሥረዓት አለመኖር፤

5.3 - ኤች አይ ቪን በተመለከተ በቂና ተገቢ የሆነ የሰው ኃይል በየደረጃው አለመሟላትና አስፈላጊውን በጀት አለመመደቡ፤

5.4 - በየጤና ተቋማት በቂ የሆነ የኤች አይ ቪ ኤድስ መመርመሪያ የላቦራቶር መሣሪያዎችና ኪቶች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፤

5.5 - በኤች አይ ቪ ኤድስ ቅድመ ደም ምርመራም ሆነ ድህረ ደም ምርመራ የሚሰጥ የምክር አገልግሎትና ክትትል ጠንክራ አለመሆን፤

5.6 - በኤች አይ ቪ ኤድስ ተጠቂ ለሆኑ ሕመሞችንና ቤተሰቦቻቸው የሚደረገውን እንክብከቤ ከችግሩ ስፋት አንፃር ሲታይ አናሳ መሆኑን፤

5.7 - በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት ድጋፍ የሚሰጡ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በበቂ ሁኔታ አለመኖርና ያሉትም ቢሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች እንቅስቃሴአቸው ውስን መሆን፡

CCRDA

5.9 - ለኤድስ ቫይረስ በከፍተኛ ደረጃ ለተጋለጡት የሕብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት በመስጠት ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን በመቀየስ አለመንቀሳቀስ

5.9 - ከበሽታው ስርጭት ፍጥነት ጋራ የተገነዘበና ገጠሩን ያከተተ በጥናት ላይ የተመሠረተ የመከላከል መርሃ ዕቅድ አለመኖር፡

፩ በድሬዳዋ ኤች አይ ቪ ኤድስ እንዲስፋፋ ከደረጉት ምክንያቶች ዋናዋናዎቹ

በክልሉ ከሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ እንደሚገኝ ይታወቃል። መጠነ ብዙ የሆነ ወጣት በስራ አጥነትና በጐዳና ተዳዳሪነት ይታያል። ከበርከታ ክልሎች ለሴተኛ አዳሪነት ወደ ድሬዳዋ የሚመጡ የተለያየ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሴት እህቶቻችን ባህሪ ላይ የሚያደርሱት ተዕዕኖ የሚናቅ አይደለም። የሕብረተሰቡ ድህነት ከምንም የመጣ ሣይሆን ከቤተሰብ መፈናቀል ከኑሮ ዝቅተኛ ነትና በኑሮ አማራጭ አለማግኘት በተለይም ወጣቱ ምንም አይነት የመዝናኛና አእምሮውን ማሳረፊያ አጋጣሚ አለማግኘትም ጊዜውን በአልባሌ ቦታ እንዳያሳልፍና ለአደጋ እንዲጋለጥ ሆኖአል።

በክልሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ ደመጣው የጫት ቃሚ ቁጥር መጨመር ጋር አብሮ ከሚዘወተረው የመጠጥ ልማድ ጋር ወጣቱን ለዚህ አደገኛ በሽታ መጋለጥ ያለውን እድል ይጨምረዋል።

ድሬዳዋ አዲስ አበባን ከጂቡቲ ሪፑብሊክ ጋር የሚያገናኘው የባቡር መስመር የሚያልፍባትና የሚከለልባት ከተማ በመሆኒ በርከታ የንግድ እንቅስቃሴ ይከሄድባታል። ከባቡሩም በተጨማሪ የዓለም አቀፍ የአይሮኘላን ማረፊያ በመኖሩ ቁጥሩ በቀላሉ የማይገመት ህዝብ ይወጣል ይገባል። እጅግ በርከታ የሆኑ የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርከሪዎች ከተለያዩ ክልሎችና ከጐረቤት አገር ይገባሉ ይወጣሉ። እንደክልሉ የጤና ጽ/ቤት ሪፖርት መሰረት በ1992 ዓ.ም ብቻ 5197 መንገደኞች መግባታቸውና መውጣታቸው ይታወቃል።

ከላይ መግለጽ እንደተሞከረው ለበሽታው መስፋፋት አመቺ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ የሆነው ከፍተኛ የሕዝብ ዝውውር ይታያል። ለኤች አይ ቪ መስፋፋት አመቺ የሆነው ልቅ የግብረስጋ ግንኙነት አስመልክቶ መንስዔው በውል ባይታወቅም ድሬዳዋ ባላት የንግድ ማእከለነት ሳቢያ ያሚንቀሳቀሰው ሕዝብ በባሕሪ ለውጥ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ በድሬዳዋ ወጣት ሴቶች የመጀመሪያ የግብረስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙት ገና በለጋነት ዕድሜ(በ13 ዓመት) መሆኑ ለኤች አይ ቪ መጋለጥ ሌለኛው ምክንያት ነው።
የአባለዘር በሽታዎች ቁጥጥር በጤና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ በአግባቡ ያልተቀናጀና ለዚህ አግባብ ባለው መልኩ ያልተደራጀ መሆኑ ለበሽታው መዛመት ከፍተኛ የሆነ ስነህይወታዊ ክፍተት ይፈጥራል። ከለው የጤና አገልግሎት ብቃት አናሳነት ጋር በአሁኑ ወቅት ያለው የወሊድ መከላከያ አገልግሎት የቅድመ ወሊድና ወሊድ አገልግሎት ዝቅተኝነት ከእናት ወደ ጽንስ የሚኖረውን የበሽታ መተላለፍ ዕድል ይጨምረዋል።

ጐጂ የሆኑ ልማዳዊ ተግባሮችን አስመልክቶ በክልላችን በርከታ ሕዝብ በሴት ልጆች ላይ ግርዛት መፈጸሙ የሚታወቅ ብቻ ሳይሆን የግርዛት አፈፃፀሙ በአይነቱ እጅግ አደገኛ መሆኑ ችግሩን የበለጠ ያወሳስባል።

CCRDA

ሲላው እንደማንኛውም የሐገራቱ አከባቢዎች ለኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ምቹ ሁኔታን የፈጠረው ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው በኤድስ ዙሪያ የግንዛቤ ማዳበሪያ ትምህርት አቀራረብ የፈጠረው አሉታዊ ተጽእኖ በሕብረተሰቡ ዘንድ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን የማግለልና የመሸሽ ችግር ከመፈጠሩም በላይ ስለጉዳዩ በግልጽ ለመወያየት አለመፍቀድ ዝምታው እንዲጠናከር አድርጉታል።

7. የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በድሬዳዋ ያለ አመቺ ሁኔታ ምን ይመስላል?

የአስተዳደር ክውንስሉ የቆዳ ስፋት አነስተኛ መሆን

አመቺ የመገናኛ አውታሮች መኖራቸው

በሴክተር መ/ቤቶች መከከል መልከም የስራ ትብብር እና ግንኙነት መኖር

በርከታ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ድርጅቶች መኖር

ማህበራዊ መሰረተ ልማት (ትምህርት ጤና ውሃ ወዘተ...) በገጠርና በከተማ የተሻለ መሆን

የሕዝቡ ባህሪ በንጽጽር በግልጽ ለመወያየትና ለመናገር ያለው ፍላጐትና ችሎታ

መረጃን ለመለዋወጥ በንጽጽር መንገዶቹ የተሻሉ መሆናቸው

አብዛኛው የከተማ ነዋሪ (82 በመቶ ያህሉ) ማንበብና መፃፍ መቻል

8. በድሬዳዋ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም ድጋፍ ለመስጠትና ለመንከባከብ የታሰቡ ኘሮግራሞች ምን መሆን አለባቸው?

በጋራ ጥረት ኤድስን ለመከላከል የተደራጁ ተቋማትን አቅም ማጠናከር።

ይሽም ከክልሉ ሴክሬታሪያት ጀምሮ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ በሰው ኃይል በማቴሪያልና በስልጠና አቅም ማጐልበትን ያከትታል።

ብዙ ዘርፎችን በማከተትና በማቀናጀት ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንደዚሁም ድጋፍና አንክብከቤ ለማድረግ ማቀድ መተግበርና ስለአፈፃፀሙ መከታተል።

ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ኘሮግራም ማከሄድ፡
የአባለዘረ በሽታዎች መከላከልና ሕክምና
በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግ፡
የኮንዶም አጠቃቀምና ስርጭት

CCRDA

ለሕክምና ተቀጣሚነት ለኤች አይ ቪ ኤድስ ስራ ላይ በሚደረጉ ሁለንተናዊ አድማሳዊ (ዩኒቨርሳል ኘሪኩሽን)

ደህንነቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦት

ሕብረተሰቡን በማክሰ ሁኔታ አስተማማኝ የሆነ ድጋፍና እንክብከቤ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩና ቤተሰቦቻቸው እንደዚሁም ወላጅ አልባ ሕፃናት ማድረግ

ከህክምና ተቀጣሚነት ውጪ ጉጂ በሆነ ባህላዊ ልምድ ምክንያት በደም ንክኪ መተላለፊያ መንገድ ማስወገድ፡

ኤች አይ ቪ ኤድስ ሊያመጣ የሚችለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ለመቀነስ መንቀሳቀስ፡

መረጃን ማሰባሰብና ምርምር ማከሄድ

ከእናቶች ወደ ሕፃናት የኤች አይ ቪ መተላለፍን መከላከል

በክልል ደረጃ በስልጠና ላይ በመመስረት ሰርቬላንስ ማጠናከር

በያታ አኩልነት ላይ የተመሠረተ የኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ስራ በስፋት ማከሄድ፡

9 ኘሮግራሙን ለመፈጸም ትኩረት የሚሰጣቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች

- ወጣቶች
- ሴቶች
- እናቶችና ህፃናት
- ሴተኛ አዳሪዎች
- የረጅም ርቀት ከባድ መኪና አሽከርካሪዎች
- ያሕዝብ ማመላለሻ፣ መኪና፣ ጉዞ ጠርጣሪዎች
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች
- ወላጅ አልባ ህፃናትና ወጣቶች
- ሌሎች

CCRDA

10. መርሀ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገልግል አደረጃጀት /ኢንስቲቱሽናል ፍሬም ወርክ/

ብዙ ዘርፎች የሚሳተፉበት ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራም አስፈፃሚ አከላት ከዚህ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

_ መንግስታዊ ድርጅቶች
_ ሕዝባዊ ድርጅቶች
_ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
_ የግል ድርጅቶች
_ የሃይማኖት ተቋማት
_ እና የመሣሠሉትን የሕብረተሰብ ክፍሎች ያቀፈ ነው፡፡

የፕሮግራሙን ዓላማ ለመተግበር

በክልል ደረጃ፤

_ የድሬዳዋ አስተዳደር ከውንስል ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት
_ የድሬዳዋ አስተዳደር ከውንስል ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት
_ አማከሪ ቦርድ (አድቫይዘሪ ቦርድ)
_ የቴክኒክ ሪቪው ቦርድ
_ የወረዳ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከ/ መቆ/ ምክር ቤት
_ በቀበሌ ደረጃ ፀረ ኤድስ ኮሚቴ
_ በየቀበሌው የሚገኙ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የግልና ሕዛባዊ ድርጅቶች እንደዚሁም የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ያከትታል፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር ከውንስል የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የክልሉ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም መምራት ማስተባበር
2. ስለኤች አይ ቪ ኤድስ ግንዛቤ ማዳበር አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጠው ማነሳሳት ማሳወቅ

CCRDA

3. ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አመቺ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት
4. ኤች አይ ቪ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ፕሮጀክቶችን ፕሮግራሞችን አፈፃፀም መከታተል መገምገም ዓመታዊ ሰቅዶቹና በጀት መመደብ መፍቀድ።

ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን እንዲያስችለው የክልሉ ኤች አይ ቪ ኤድስ ከውንስል በአማከሪ ቦርዱና በሪቪው ቦርድ ይታጋዘል። ሞያዊ ምክርና የውሳኔ ሀሳብ ያገኛል።

- የድሬዳዋ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት የሚያቅፋቸው አባላት፤

  _ የአስተዳደር ከውንስሉ ሊቀመንበር በሰብሳቢነት የሚመሩት
  _ የሴክተር መ/ቤቶች ሃላፊዎች
  _ የሃይማኖት አባቶች
  _ መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ ተቋማት
  _ የግል ድርጅቶች
  _ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች
  _ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ክፍሎች ያከትታል:

CCRDA

3. የአማከሪ ቦርዱ ስብጥርም ከላይ ከተጠቀሱት መ/ቤቶች ድርጅቶች ተወከይችን የያዘ ነው ::

_ የሪቪው ቦርዱ አመሰራረት መሰረት የሚያደርገው

- የሞያ ብቃት
- ኘሮጀክቶችን የመገምገም ችሎታና ልምድ ሆኖ በተቻለ መጠን የሚከተሉትን አከላት ያከትታል::
  - _ ከከውንስሉ አባላት
  - _ ከሴክተር ጽ/ቤት
  - _ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
  - _ የግል ድርጅት
  - _ የሞያ ማህበራት ተወከይ

_የአማከሪ ቦርድ ዓላማ በክልል ደረጃ ያሉት የም/ቤቱን ሥራ በውክልና ያከናውናሉ፤ ሪፖርት (ለም/ቤቱ) ለከውንስሉ ያቀርባሉ::

_ የሪቪው ቦርድ ተግባር ለሚኖረው የሥራ ድርሻ

- ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍል የሚቀርቡ ኘሮጀክቶችን ይገመግማል፤
- የሚሰጡትን ጠቀሜታና ወጪ ይመዝናል፤
- የኘሮጀክቶቹ ጠቀሜታን በመመዘን ተግባር ላይ እንዲውሉ ሀሳብ ያቀርባል፤
- በክልል መ/ቤቶች ስለሚቋቋሙ አከላት፤
- በመንግስት መ/ቤቶች፤
- አንድ ተጠሪ ይኖራል፤
- ከሶስት ያላነሱ አባላት ያሉት ግብረ ሃይል ይቋቋማል::

CCRDA

4 በክልል ም/ቤቶች ሥር ደግሞ፤

- ስክሬታሪያት፤
- ፕሮግራም ኦፊሰር፤
- ፋይናንስ ኦፊሰር ይመደባሉ፤

እነዚህም በክልል ደረጃ የፕሮጀክቱ ማስተባበር ሥራ ያከናውናሉ።

_ የክልል ሴክሬታሪያት

_ እንደ ደንሮጀክት አስተባባሪ በመሆን ያገለግላል። የሚመደቡትም በክልሉ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ ም/ቤት ሆኖ በችሎታና በልምዱ ላይ የተመሰረተ ይሆናል

- ፕሮግራሙ ኦፊሰሩና ፋይናንስ ኦፊሰሩ የሚመደቡት (የሚቀጠሩት) ለሥራው ይሆናል፡

- አቀጣጠሩም (አመዳደቡም)።

- በውድድር ላይ ተመስርቶ፡

- ብቁ ሞያ ያላቸው፡

- በፕሮጀክት ሥራም ልምድ ያከበቱ መሆን ይገባዋል።

_ በወረዳና በቀበሌ ደረጃዎች በወረዳ ም/ቤት ሥራ ሥራውን የሚያስተባብሩና ሂሳቡን የሚይዙ ባለሞያዎች ይመዳባሉ (ይቀጠራሉ)

11. ክትትልና ግምገማ

በየደረጃው የሚከሄደውን ኤች አይ ቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች ክትትል እና ግምገማ እንዲከሔድ ይደረጋል።

CCRDA